Ethiopia update

A monthly publication of the Embassy of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, Stockholm

# የመልካም ምኞት መግለጫ

**ግንቦት 12 ቀን 2002 ዓም**

በሀገራችን የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታና ህገ-መንግስታዊ ስርአት መዘርጋት ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ ሶስት ተከታታይ ሀገራዊ ምርጫዎችን ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ አካሂዳለች፡፡ እነዚህ ምርጫዎች ዜጎች በሀገሪቱ ህገመንግስታዊ ድንጋጌዎች የተጎናፀፏቸውን የመምረጥና የመመረጥ መብቶች ሙሉ በሙሉ እንዲተገብሩና በተጨባጭ ተግባራዊ ሂደትም እንዲረጋገጥ አድርገዋል፡፡ በአሁኑ ወቅትም ለአራተኛ ጊዜ በሚካሄደው ብሄራዊ  አገራዊ ምርጫ ዋዜማ ላይ እንገኛለን፡፡

ባለፉቱ ሶስት ተከታታይ ምርጫዎች መራጩ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ፣ ግልፅና ሰላማዊ በሆነ ሂደት በየደረጃው ይበጁኛል የሚላቸውን የህዝብ ተወካዮች በመምረጥ ለሀገራችን የመድበል ፓርቲ ስርአት ግንባታ የበኩሉን ታላቅ አስተዋፅዎ አበርክቷል፡፡ በዚህም ለሀገራችን ጅምር የዲሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ሂደት ታላቅ መሰረት ተጥሏል፡፡ በይበልጥም ተጠናክሮ በመገንባት ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህ ባሻገር በሀገራችን የመንግስትና የህዝብ ስልጣንን በሰላማዊ መንገድና በዲሞክራሲያዊ ምርጫ ማሸጋገር የሚችልበትን ሂደት መፈጥሩን አረጋግጧል፡፡ ይህንን ብሩህና ጅምር የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሂደትን በማጎልበት ቀጣይነቱን ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ ደግሞ ምንም ጥርጥ የለውም፡፡

በመሆኑም መጪውም የ2002 ሀገራዊ ምርጫ መላው ህዝብ በተለይም ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ምርጫውን ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መልኩ አካሂደው እንዲጠናቀቅ የሚያደርጉበት፣ የመራጩን ህዝብ ድምፅ በማክበርና ይዘቱ ምንም ይሁን ምን የምርጫውን ውጤት በፀጋ በመቀበል ለህዝብ ምርጫ ያላቸውን ከበሬታ በቁርጠኝነት የሚቆሙበትና በተግባርም የሚያረጋግጡበት እንዲሆን እንመኛለን፡፡

ለሀገራችን ሰላምና እድገት ቀጣይነት፣ ለዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታችን መጎልበትና ማደግ ከምንም በላይ ሁሉም የምርጫ ተሳታፊ ወገኖች የመራጩን ፍላጎትና ምርጫ አክብረው ለመቀበል እንዲሁም አንዱ ወገን የሌላውን ወገን ምርጫ ለማክበር ዝግጁ መሆን እንዳለባቸው እሙን ነው፡፡ በዚህ ረገድም መጪው ምርጫ ዲሞክራሲያዊና መላው የሀገራችን ህዝቦች፣ ብሄሮችና ብሄረሰቦች በሙሉ ፍላጎትና ፍቃደኝነት ላይ ተመስርተው ይበጀኛል የምትሉትን የህዝብ ተወካይ ግልፅ የሚመርጡበት፣ ታአማኒና በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያለውና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ተካሂዶ ለሀገራችን ሰላምና ልማት ቀጣይነት መረጋገጥ ፋይዳ ባለው መልኩ የሚጠናቀቅበት ምርጫ እንዲሆን መልካም ምኞታችንን ለመላው የሀገራችን ህዝቦች እንገልፃለን፡፡

የኢትዮጵያ ኤምባሲ

ስቶክሆልም